# የወገን ደራሽ ወገን ነው!!

## ታላቅ ህዝባዊ የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ

## በዋሽንግተን ዲሲ የሳውዲ ዓረቢያ ኤምባሲ ፊት ለፊት

የሰልፉ አንገብጋቢነት፣ መነሻና አላማ፡- ሰሞኑን በተለያዩ የብዙሃን መገናኛዎች እንደተገለፀው ሁሉ በሳውዲ ዓረቢያ በተለያዩ ከተሞች በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ላይ የደረሰውና አሁንም በባሰ መልኩ እየተፈፀመ ያለው አስነዋሪ፣ አሳዛኝ፣ አሳፋሪና አስደንጋጭ የሆነ ኢሰብአዊ ድርጊትን በመቃወም፡-

1. የሳውዲ ዓረቢያ አረሜናዊ መንግስት በወገኖቻችን ላይ እየወሰደ ያለው የግድያ፣ በእስር የማሰቃየትና የማንገላታት እርምጃ በማውገዝና ድርጊቱንም በአስቸኳይ እንዲቆም መልእክታችንን ለማስተላለፍ ነው።

2. ይህ እርምጃ የዓለም አቀፍ የሰብኣዊ ፍጡር ነፃነት ድንጋጌዎችን የሚጥስ ሕገ ወጥ ተግባር በመሆኑ የዓለም ማሕበረሰብና ሰብኣዊ መብት ተሟጓች ድርጅቶችና ተቋሞች ሁሉ የጉዳዩን አሳሳቢነትና ጥሰት በመገንዘብ ለችግሩ መፍትሔ አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርጉ ጥሪ ለማቅረብ ነው።

### <u>የተከበራችሁ ውድ ኢትዮጵያውያን ሆይ!!</u>

"ባለቤቱ ያቃለላት ሂይወት..... ባለዕዳ አይቀበላትም" እንዲሉ በገዛ ሀገሩ እንደ ባይተዋር ተቆጥሮ፣ ነፃነቱ፣ ሰብኣዊ ክብሩንና ማንነቱን ተነጥቆ፣ አውራ እንደሌለው ንብ ስደት እንደ አማራጭ ወስዶ ራሱን ዝቅ አድርጎና ተበታትኖ የሚኖር ህዝብ በሚረባና በማይረባ ሀይል እንደ አራዊት እየታደነ ሲቀጠቀጥ ዝም ብሎ እየታየ ቆይቶ አሁን አሳሳቢ ሁኔታ ላይ መድረሱ እሙን ነው። "የሰው ልጅ ሞተ የሚባለው መቃብር ከወረደ በኋላ አይደለም። ሞት የሚጀምረው እንደ ሰው ለመኖር የሚያስችለው ሞራል፣ ማሰብና ማድረግ ሲያቆም ነው" ብለዋል የነፃነት ታጋዩ "ማልቲን ሉተር ኪንግ"። ታዲያ!! አንገታችንን ደፍተን ዝም በማለት የዓረብ ቱጃሮች መጫወቻ እንድንሆን በገዛ ራሳችን ስለፈቀድንላቸው ለዚህ ሁሉ ዕልቂትና መከራ ተዳርገናል። ስለሆነም ሁላችንም በኢትዮጵያዊነት ጥላ ስር ቆመን ቆፎው እንደተነካ ንብ በቁጣ አደባባይ ወጥተን ለያንዳንዳችን ነፃነት፣ ማንነትና ክብር ስንል አኩሪ ታሪክና ወርቃማ ባህል ያለን ህዝብ መሆናችንን ለሳውዲ ሰው በላ መንግስት ብቻ ሳይሆን ለዓለም ህዝብም ካላሳየን በስተቀር ማንም ጥብቅና ሊቆምልን የሚችል ሀይል አይኖርም። ይህም የአሁኑ ትውልድ መመለስ ያለበት የጋራ ሃላፊነት ነው ብለን እናምናለን።

አዎ!! እኛ ኢትዮጵያውያን በአፍሪቃ አህጉር የነፃነት፣ የኩሩና የአትንኩኝ ባይ ጥቁር ህዝብ ተምሳሌት ተብለን በዓለም ታሪክ እንዳልተመሰከረልን ሁሉ ዛሬ መሬታችንንና አንጡራ ሀብታችንን በሳውዲ ቱጃሮች መወረሩንና መዘረፉን ሳያበቃ ሀገርና መንግስት እንደሌለን ተቆጥረን ወገኖቻችንን እንደ ርካሽ ዕቃ ሲጣሉ፣ በአደባባይ ሲገረፉ፣ በጥይት ተደበድበው ደማቸው ደመ ከልብ ሆኖ ሲቀር፣ እስር ቤት ሲበሰብሱ፣ ንብረታቸው ሲነጠቁ፣ ሰብእዊ ክብራቸው ተደፍሮ ባዶ እጃቸው ሲባረሩ ማየቱና መስማቱ እንደ ግለሰብ ብቻ ሳይሆን እንደ ህዝብም እንደ ሀገርም ተንቀናል ተዋርደናልም። ኢትዮጵያ የዜጎችዋን ድህንነት የሚጠብቅ መንግስት አላት ወይ ብሎ ደፍሮ ለመናገር ሀፍረት የሆነበት ጊዜ ላይ ነን ያለነው። ዛሬ የሰው ልጅ በሰለጠነበትና መብቱን ለማስከበር ግሎባል መነቃቃት በተፈጠረበት በአሁኑ በሃያ አንደኛ ክፍለ ዘመን ላይ ሆኖ ዘመናዊ ባርነትንና ውርደትን አሜን ብሎ የሚቀበል ትውልድ እስካለ ድረስ ደግሞ አደጋው እንዳየነው ሁሉ ከዚህም የባሰ ሊመጣ እንደሚችል አያጠራጥርም።

ስለዚህ በየአካባቢያችን በሳውዲ ዓረቢያ ኤምባሲ ፊት ለፊት የምናደርገው ሰላማዊ ሰልፍ የፓለቲካ ወይም የአንድ ቡድን ሰብኣዊ ርህራሄ ጉዳይ ሳይሆን ሁላችንም የሚመለከት የኢትዮጵያዊነት ግዴታም ጭምር ነው። በመሆኑም ያለንን መለስተኛ ልዩነቶች ወደ ጎን ትተን ወገኖቻችንን ከችግር ለማዳን "**ውርደት ያብቃ**" ብለን ከጎናቸው በመቆም በጋራ አደባባይ ወጥተን አቤቱታችንን እንድናሰማ ጥሪያችንን ከታላቅ አክብሮት ጋር እናቀርባለን።

**ቀን** ፡- ኖቨምበር 18, 2013 ዕለተ ሰኞ ከጥዋቱ 9 ሰዓት በኤምባሲው ፊት ለፊት ይጀምራል።

**አድራሻ**፡- 601 New Hampshire Avenue NW, Washington DC 20037

**Public trasport**:- Foggy Bottom metro station – Blue and Orange line

ዋሽግንተን ዲሲና አካባቢያዋ በሚኖሩ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በጋራ የተዘጋጀ